# የግዜያዊ ግንባታ ዋና አማካሪ መልእክት

ብስራ ሓላፊነት ለአምስት ወራት ከቈየሁ በኋላ ዛሬ እንደ የግዜያዊ ግንባታ ዋና አማካሪ (CCA) ይህንን መልእክት አስተላልፋለሁ። መስከረም 30 2025 ነበር የተሾምኩት የስራ ድርሻዬም በግንባታ ደሕንነት እና የቁጥጥር ለውጥ ላይ ለመንግስት ገለልተኛ ምኍት፣ ቁጥጥር እና ምክር መስጠት ነው።

የስራ ድርሻው እንዲኖር በግሬንፌል ታወር ማጣሪያ ምክረሃሳብ ላይ ቀርቧል፤ በዚህም የፓናል አባል በመሆን ተሳትፌያለሁ እንዲሁም የግንባታ ግዜያዊ ዋና አማካሪነት ሓላፊነቴን ተቀብያለሁ። ማጣሪያው ግሬንፈል ታወር፡ የ72 ንጹሃን ሰዎች ህይወታቸውን እንዲያጡ ያደረገ አሰቃቂ ፍጻሜ መሆኑን ተገንዝቧል እንዲሁም፡ "ለአስርት ዓመታት ሲከማች የነበረ እና በማእከላይ መንግስት እና በግንባታ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሓላፊነት የተሸከሙ ሌሎች አካሎች በተፈጸሙ ጉድለቶች ውጤት ነው።"[1] ከአሰቃቂው ፍጻሜ በኋላ በሺዎች የሚቈጠሩ ለደህንነት አስጊ እና ድጋሚ መስተካከል የሚያስፈልጋቸው ርብራቦች የተገኙባቸው ደህንነት ያልተሟላባቸው ብዙ ህንጻዎች ተገኝተዋል። የኔን ገለልተኛ የስራ ድርሻ፡ ከግንባታ ደህንነት እና የቁጥጥር ለውጥ ጋር በተያያዙ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ለመንግስት ምክር በማገዝ እንደ አንድ አስፈላጊ ድምጽ አየዋለሁ።

የስራ ድርሻዬ ገለልተኛ ነው እንዲሁም እኔ የኢንዱስትሪ ወኪል አይደለሁም። በተጨማሪም ሌሎች አካላት ማበርከት የሚችሉት አስፈላጊ አስተያየቶች እንዳላቸው እረዳለሁ። በዚህም፡ የኔን ገለልተኛ ምክር ለመደገፍ ሰፊ አስተያየቶችን የማቅረብ ፍላጎት አለኝ። ካለኝ የመጀመሪያ ደረጃ ልምድ በመነሳት፡ የደሕንነት ተግባሮችን ማሻሻል፡ቢዝነሶች፡ የብቃት ደርጃዎቻቸውን ለማሳየት እንዲሁም ለደንበኞች ከፍተኛ ደረጃ ጥራት እንዲያቀርቡ ዕድል የሚያስገኝላቸው እንደሆነ አውቃለሁ። በተጨማሪም በግንባታ ኢንዱስትሪ ውስጥ የምንሰራ ሁላችንም፡በምናደርጋቸው ነገሮች ህንጻዎች ውስጥ የሚኖሩ እና የሚሰሩ ሰዎችን ማእከል የማድረግ የስነምግባር ግዴታ አለብን።

በስራ ቁይታዬ ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው ነገሮች ከግንባታ ደህንነት ሚኒስትር ጋር ተስማምቻለሁ። የስራ ግዜዬ ወደ ማብቃቱ ሲቃረብ፡ የስራዬን ሙሉ ሪፖርት የማቅረብ ሓሳብ አለኝ። በተጨማሪም፡ እኔን ለሚተካ ሰው በተገቢ ሁኔታ አስረክባለሁ። ዛሬ መንግስት፡ የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ያቀረባቸውን ምክረሃሳቦች ለመተግበር አያደረገ ስላለው ይሚገልጽ አመታዊ ሪፖርት ላይ፡ በአመቱ መጨረሻ ላይ ዋና የግንባታ እና ሳይንሳዊ አማካሪ (CCSA) ለመሾም ዕቅድ እንዳለው መግለጹን አስተውያለሁ።

## የስራ ጊዜዬ ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች

ቅድሚያ የምሰጣቸውን ጉዳዮች ለመምረጥ፡ የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች እንዲሁም ይህን ተከትሎ በሰፊው የግንባታ ዘርፍ የታዩትን ድክመቶች እንደግብአት ተጠቅሚያለሁ። በማጣሪያው የተጋለጡት ድክመቶች እና ተያያዥ ምክረሃሳቦች እንዲሁም ይህን ተከትሎ የታየው ለደህንነት አስጊ ርብራቦች (ክላዲንግ) እና በሺዎች የሚቆጠሩ ህንጻዎች ላይ የታዩት የደህንነት ስጋቶች፡

[1] የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ፡ ደረጃ 2 ሪፖርት፣ ቅጽ 1፣ ምዕራፍ 2፣ ነጥብ 2.4, ገጽ 9

ለመንግስት በምሰጠው ምክሮች ላይ አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው። ሲያስፈልግ ስርዓቱን የተከተለ ለውጥ እደግፋለሁ።

ማእከላይ መንግስት እና ሰፊው የግንባታ ኢንዱስትሪው የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ያስገኛቸው ማስረጃዎች ሲሰሩ፡ ብዙ ሰዎች የከስሯቸውን ነገሮች የግድ መርሳት የለባቸውም። ቤተሰቦችን ያጡ፣ ከአደጋ የተረፉ እና ሰፊው የግሬንፌል ማሕበረሰብ እንዲሁም ደህንነት በሌላቸው ህንጻዎች ውስጥ ለሚኖሩ እና ለሚሰሩ ሰዎች፡ ከግሬንፈል ታወር አስከፊ ፍጻሜ የተማረ፣ ለደህንነት አስጊ ህንጻዎችን የሚጠግን እና ለወደፊቱ ደህንነት የሚሰጥ አሰራር የማቅረብ ዕዳ አለብን። የአዳዲስ እና አሁን ያሉ ህንጻዎችን ደህንነት እና ጥራት የሚያሻሽል እንዲሁም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እና ተራማጅ ለውጥ ልንፈጥር ይገባል። ይህንን በማድረግ፡ የህንጻ ነዋሪዎችን እና ተጠቃሚዎችን የሃሳቦቻችን ማእከል ልናደርጋቸው ይገባል። ዎች ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ እንዲኖሩ እና እንዲሰሩ ለማድረግ፡ ህንጻ ውስጥ እና ከህንጻ ውጪ ያላቸውን ፍላጎቶች ግምት ውስጥ በማስገባት አለብን።

ማስረጃዎቹን ፣ ከብዙ እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያአረግኩትን ግንኙነት እንዲሁም እንደ አርክቴክት ያካበትኩት ልምድ መነሻ በማድረግ በስራ ቆይታዬ ቅድሚያ የምሰጣቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡

- የግንባታ ውጤቶች ቁጥጥር ለውጥ፣
- የህንጻዎች ግንባታ እና በግንባታ የሚሳተፉ ባለሙያዎች የብቃት ደረጃ፣
- ከአደጋ ለጥቂት ማምለጥ ከተቻለባቸው ክስተቶች የሚሰበስቡ ማስረጃዎች እና ትምህርቶች፣
- የዋና የግንባታ እና ሳይንሳዊ አማካሪ (CCSA) ቋሚ የስራ ድርሻ እንዲኖር መደገፍ።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ለማድረግ ወስኛለሁ ምክንያቱም፡ የግንባታ ዘርፉ መሰረትን የሚወክሉ እና የላቀ ተጽእኖ እፈጥርባቸዋለሁ ያልኳቸው ናቸው። አሁን ባሉት ህንጻዎች ላይ ያሉትን ችግሮች ለማስተካከል እንዲሁም አዲስ ህንጻዎች ቀጣይነት ባለው ከፍተኛ ጥራት ደረጃ እንዲገነቡ ማድረግል ውጤታማ ቁጥትር እና አፈጻጸምእንዲሁም በግንባታ ኢንዱስትሪ ውስጥ ባልው ባህል እና ጸባይ ላይ ይመረኰሳሉ ። መሻሻልን ለመደገፍ የራሴን ድርሻ እወጣለሁ።

እስከአሁን ድረስ፡ በመንግስት እና የግንባታ ዘርፍ ተሳትፌያለሁ። ከግንባታ ደህንነት ሚኒስተር ጋር ቀጣይ ግንኙነት አለኝ። ከቤቶች፣ ማህበረሰብ እና አካካቢ መስተዳድር ሚኒስትር ሓላፊዎች ጋር ተነጋግሬያለሁ፣ ከአንዲ ሮ፣ የግንባታ ደህንነት ተቆጣጣሪ (BSR) ሊቀመንበር እኛ ቻርሊ ፐግስሊ፣የ ቢ ኤስ አር ዋና ስራአስኪያጅ ጠንካራ የስራ ግንኙነት መስርቻለሁ እንዲሁም በጤና እና ደህንነት ስራ አስፈጻሚ ዋና የሳይንስ አማካሪ ከሆነው አንድሪው ኩራን ጋር ተነጋግሬያለሁ። ከመንግስት ውጪ፡ ከኢንዱስትሪው እና ሌሎች የግል ግንባታእና ሌሎች ፎረሞች ባለድርሻ አክላት ጋር ተገናኝቻለውሁ ለምሳሌ የኰንስትራክሽን ሊደርሺፕ ካውንስል እና ቢዩልድ ዩኬ አባላት ጋር። በግንባታ ደህንነት እና የቁጥጥር ለውጥን አስመልክቶ ስለቀደመው እና የአሁን ስራዋ ለመነጋገር ከዴም ጁዲት ሃኬት ጋር ተገናኝተናል። በተጨማሪም፡ ዋና የግንባታ አማካሪ ሆኖ ሲስራበት ስለነበረው ድርሻ እና ልምድ እንዲሁም በግንባታ ውጤቶች ፍተሻ ገለልተኛ ገምጋሚነት ስለ ሰራው ስራ ለመነጋገር ከፖል ሞረል ጋር ተገንኝተናል።

**ቀጣይ እርምጃዎቼ**

በቀሩኝ የስራ ግዜያት፡ ትኩረቴ ቅድሚያ የሰጠኋቸውን ማስቀጠል እና የመንግስት ፖሊሲ ቅርጽ ማስያዝ ላይ ለማገዝ ገለልተኛ ምክሬን መስጠት ላይ ይሆናል። በተጨማሪም ግንኙነቴን ለማስፋት ፍላጎት አለኝ። እንደ የህንጻ ደህንነት ተቆጣጣሪ የነዋሪዎች ቡድን ካሉ ቡድኖች ጋር የምገናኝበትን እንዲሁም በግንባታ ደህንነት እና የቁጥጥር ለውጥ ላይ ያተኰሩ የህዝብ ክርክሮች ክፍለጊዜዎች ላይ የምሳተፍበትን ግዜ እጠብቃለሁ። ይህንን ግንኙነት ፡ተጨማሪ መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ምክሮቼን ቅርጽ ለማስያዝ ግብአት ለመሰብሰብ እና ገንቢ በሆነ መንገድ ለመሞገት እጥቀምበታለሁ።

መስከረም 2026 ላይ የስራ ጊዜዬ ሲያበቃ፡ በጊዜዬ እንደ ግዜያዊ ግንባታ  ዋና አማካሪ ያደረኳቸውን ስራዎች የሚዘረዝር ሪፖርት የማዘጋጀት ሃሳብ አለኝ። በግንባታ ደህንነት እና የቁጥጥር ለውጥ ላይ መሻሻል እንዲኖር የድርሻዬን ሚና በመጫወቴ ክብር ይሰማኛል። ያለኝ ግዜ የተገደበ ሆኖ ሳለ፡ ለሚመጣው  ዋና የግንባታ እና ሳይንሳዊ አማካሪ (CCSA) መሰረት ለማዘጋጀት እንዲሁም ተመጣጣኝ እና ገስጋሽ አቀራረቦችን እና ተነሳሽነቶች እንዲኖሩ ለማድረግ ይህንን ዕድል ለመጠቀም ተግቼ እሰራለሁ።